# ለምን ይመለካሉ?

ከተንሳይት በቃና

ማርች 18 ቀን 2016 ዓ.ም.

ባሁኑ ባለንበት ሃያ አንደኛው ክፍል ዘመን ያሉት አገሮች መንግስታት እንዳሏቸው እንገነዘባለን።“መንግስት የመጨቆኛ መሳሪያ ነው“ በማለት አገሩ ውስጥ ያሉትን ያአገሪቱን ተወላጆች በመደብ በመከፋፈል የተወሰኑ መደቦችን ጨቋኝ ሌሎቹን ተጨቋኝ በማድረግ የመንግስት ስልጣን የጨቋኙ መደብ መጨቆኛ መሳሪያ በማድረግ የሚጠቀሙ አገሮች አሉ። በሌላ ወገን ደግሞ የአገሪቱን ተወላጆች አንዱን መደብ ከሌላው ሳይበላለጥ በእኩልነት ለማስተዳደር የመንግስት ስልጣንን ለመጠቀም የሚሞክሩ አገሮች አሉ።

ለእኛ አቀራረብ ግን የመንግስት ስልጣን እንዴት ለአገሪቷ ነዋሪዎች በስራ እንደሚተረጎም ለማተት ሳይሆን፣ የመንግስትን ስልጣን በተለያየ መንገድ ይዘው በአገሪቱ መሪነት ያሉትን ግለሰቦች በሚመለከት ያለንን አስተሳሰብ ለማቅረብ ነው። ከአንዳንድ የማርክሲስት-ሌኒንንስትን ፍልስፍና ከተቀበሉ ምሁራን እንደተጻፈው በዓለም ውስጥ ያሉት ርዕዮተ ዓለሞች ሁለት ናቸው ብለን እነርሱ እንደሚሉት እንቀበል።

እነርሱም የከበርቴውና የላብ አደሩ ርዕዮተ ዓለም መሆናቸው ነው።የላብ አደሩ ርዕዮተ ዓለም ተከታይ አገሮች እኛ እንደሚገባን ከሆነ የአንድ ፓርቲ ሲስተም ሲከተሉ የከበርቴው ርዕዮተ ዓለም ተከታዮች አብዛኛዎቹ አገሮች ደግሞ የብዙ ፖለቲካ ፓርቲዎችንና የፓርላማ መኖርን የሚቀበሉ ናቸው። የላብ አደሩ ርዕዮተ ዓለም ተከታይ አገሮች አንድ የኮሚኒስት ፓርቲ ሲኖራቸው፣ ከፓርቲው አባላት መሃከል አንድ ግለሰብ ፓርቲውን ወክሎ ያገሪቱ መሪ ሆኖ በፓርቲው አባላትና በሌሎች እድሜያቸው ለመምረጥ የደረሱ የአገሩ ዜጎች ምርጫ ተካሂዶ እንደሚመረጥና ስልጣን እንደሚይዝ ይነገራል።ይህ ግለሰብ እድሜ ልኩን መሪነቱን እንደያዘ ይቆያል።

በመሃል በተወሰነ የግዜ ገደብ የሕዝብ ምርጫ እንዲደረግ ተብሎ ግለሰቡ መምረጥ የሚገባቸው የአገሪቱ ተወላጆች በሙሉ ድምጻቸውን ለእሱ እንደሰጡት ይነገራል።ይህ እውነትነቱ ምን ያህል እንደሆነ ራሳችንን ስንጠይቅ አልዋጥ ይለናል።አንድ ግዜ ሁለት ግዜ ሙሉ የመራጮችን ድምጽ ማግኘት ቢቻልም፣ ሰውዬው እስከሚሞት ድረስ በተደረጉት ምርጫዎች በሙሉ የመራጮችን ሙሉ ድምጽ አግኝቷል ተብሎ የሚነገረው ተራ ፕሮፓጋንዳ እንጂ ፈጽሞ እውነት እንዳልሆነ እንረዳለን።

ምክንያቱም መሪው ስልጣኑን ከያዘ ግዜ ጀምሮ ሁሉን ያገሪቱን ዜጎች ሙሉ በሙሉ አስደስቷል፣ ወይም ፍላጎታቸውን አርክቷል፣ ምንም ቅሬታ ያለው መሪውን በሚመልከት የለም፣. . . ወዘተ ማለት ስላልሆነና ብዙ ቅሬታዎችና ያልተሟሉ የህዝብ ፍላጎቶች ስለሚኖሩ በዚህ ዓይነቱ ሁኔታዎች ያንኑ መሪ መምረጥ የማይፈልጉ ይኖራሉ።ግን የግዴታ ውዴታ ስለሆነባቸው የማይፈልጉትን መሪ እንደፈለጉት አድርገው መምረጥ ይገደዳሉ።ያለበለዚያ እዚያች አገር ለመኖር ያላቸው እድል በቃ አከተመ ማለት ይሆናል።

ያንን ማንም ሰው አይፈልግምና በመንግስቱ መገናኛ ዘዴዎች ግን እሱ መሪ ለመሆን ከሌላው የአገሪቱ ነዋሪዎች በሙሉ የተለየ ተሰጥዖ እንዳለው ሰው ተደርጎ፣ የመራጮቹን ሙሉ ድምጽ ወይም **99%** ድምጽ በማግኘቱ እንደ ተዓምር ይለፈፍለታል።ነገሩን ሊሚያውቀው ግን ነገሩ ተራ እውሸት ነው። እውሸትነቱን የሚያውቀውም ለመቃወም ስለሚፈራና ስለማይፈልግ „ጎመን በጤና“ በማለት ዝም ይላል። የከበርቴውን ርዕዮተ ዓለም ተከታዮች አገሮች ውስጥ ደግሞ አንድ የአገሪቱ መሪ ከተለያዩ ፓርቲዎች መሃከል ከቀረቡ እጩዎች መሃከል የሚፈልገውን ሊመርጥ ወይም የቀረቡት እጩዎች መሃከል የቀረቡት እጩዎች በሙሉ የመራጩን ፍላጎት የማያረኩ መስለው ከታዩት ላለመምረጥ ይችላል።

ከተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች በቀረቡ እጩዎች መሃከል ከምርጫው በፊት ለመራጩ ሕዝብ ያላቸው ዓላማ በጽሑፍ፣

በንግግር፣ በቃለ መጠይቅ፣ . . . ወዘተ መልክ ያቀርባሉ።

አንዳንድ ከሕዝቡ ጥያቄዎችም ካላቸው ግዜ አንጻር ለመመለስ ይሞክራሉ።በዚህ መሰረት የሚፈልጉትን መሪ መራጩ ሕዝብ ለተወሰነ የግዜ ገደብ ይመርጣል።ከተወሰነው የግዜ ገደብ በኋላ እንደገና ያው ግለሰብ በድጋሚ ለምርጫ ከቀረበ ሊመረጥና ላይመረጥ ይችላል። ግን የአገሪቱን የመራጮች ሙሉ ድምጽ ሙሉ በሙሉ ማግኘቱ በጣም ቀላል እንዳልሆነ መናገር ይቻላል።

ሁለተኛ ግዜ በመሪነት ድጋሚ አንድ ሰው ከተመረጠ በኋላ ለሶስተኛ ግዜ በእጩነትም እንዲቀርብ የማይደረግበትም የከበርቴው ርዕዮተ ዓለም ተከታዮች አገሮችም አሉ።መራጩ ሕዝብ የማይፈልገውን መተቸትና ተቃውሞውን በቀጥታ በጽሁፍ፣ በሰላማዊ ሰልፍ፣. . . ወዘተ መግለጽ ይችላል።ይህን በማደረጉ የሚደርስበት ምንም ተጽእኖ የለበትም ማለት ባይቻልም፣ በግለሰቡ ላይ በቀጥታ የሚደርስበት ህጋዊ የሆነ ተጽዕኖ ይኖራል ብለን አንቀበልም።

ምክንያቱም ቢያንስ በሕግ የተፈቀደ ነውና። በሌላ በኩል ደግሞ በንጉሳዊ አገዛዝ ስር ያሉ የከበርቴውን ርዕዮተ ዓለም ተከታዮች አገሮች ውስጥ የአገሪቱ መሪ በምርጫ ሳይሆን፣ በንጉሳዊ ዘርነት እንደሆነና በውርስ መልክ ከንጉሱ ወይም ከንግስቲቷ ልጆች ወይም ዘመዶች መሃከል አንዱ በአልጋ ወራሽነት እንደሚቀመጡና በኋላ የመሪነት ስልጣኑን ያለ ሕዝብ ምርጫ እንደሚይዝ እንረዳለን።እንደዚህ ዓነት አገሮች ውስጥ የአገሪቷ ዜጎች መሪያቸውን የመምረጥ ሙብት ስለሌላቸው ንጉሱ እስከሚሞት ድረስ በስልጣኑ ላይ ይቆያል።ወይም በጣም ካረጀ ለአልጋ ወራሹ ስልጣኑን ሊያወርሰው ይችላል።ያለበለዚያ ግን የእድሜ ልክ መሪነቱን „ሞት ብቻ ይነቅንቀኝ“ በማለት የሙጢኝ ብሎ ይቀራል።

ንጉሱ ከእግዚአብሔር ለዚያ ሕዝብ እንደተሾመ ተደርጎ ይሰበካል።ይነገርለታልም። ባጠቃላይ ስንመለከት በዓለም ውስጥ ያሉትን አገሮች በሁለት ከፋፍለን ለማየት እንሞክራለን።ይህ ግን በአንድ ወገን የላብ አደር ርዕዮተ ዓለም የሚከተሉት የመሪዎቻቸውን አመራረጥ ሁኔታና የመሪዎቹ ስልጣን ፍጹም አንድ ዓይነት ነው ማለት እንዳልሆነና በተለያዩ ነጥቦች ላይ ልዩነት ሊኖራቸው እንደሚችል መጠቆም እንሻለን።የከበርቴውን ርዕዮተ ዓለም የሚከተሉትም አገሮች ከላይ የተጠቀሱትን ልዩነቶች የሚኖራቸው እንደሆነ እንጠራጠርም።

እንግዲህ ሁለቱን ርዕዮት ዓለሞች በሚከተሉ አገሮች መሃከል ያለውን የአገሪቱን መሪ ለመምረጥና የመንግስትን ስልጣን ለመያዝ ያለውን ልዩነት በመጠኑም ቢሆን ለመነካካት ምክረናል።የዚህም ጽሁፍ ዓላማ በዚህ ነጥብ ላይ ሰፋ ያለ ትንተና መስጠት ስላልሆነ እዚህ ላይ እንገተዋለን።

በዚህ ጽሑፋችን ትኩረት ልንሰጠው የምንፈልገው ነጥብ „የአንድ አገር መሪ በአንዳንድ አገሮች ለምን ይመለካል?“ የሚለው ሲሆን፣ ይህንን ነጥብ እንድናነሳ ያስገደዱንን ሁኔታዎች ከሞላ ጎደል ለማሳየት እንሞክራለን። ለእኛ የአንድ አገር መሪ የአገሪቱ ዜጎች ለእሱ ከሰው የበለጠ ሰው በማድረግ፣ የተለየ ተዓምር እንደሚሰራ በመቁጠር፣ በአንድ አገር የሚገኙ እድገቶች በመሪው ብቻ እንደተገኙ አድርጎ በመቀበል ፣ የመሪውን ምስል በትልቅ ካርቶን ላይ ለጥፎ በየሰልፉ በአደባባ ላይ የአገሪቱ ዜጎች እንቅፋት አይንካው፣ እሾህ አይውጋው፣ ውሎ ይግባልን፣. . . ወዘተ እንዲባልለት በተዘዋዋሪ መንገዶች በአገሪቱ ዜጎች ላይ ተጽዕኖ የሚያሳይ መሆን የለበትም።

ግን ተጨባጩ የዓለም ሁኔታ መሪዎች የራሳቸውን ገናናነት፣ ታምረኛነት፣ ትክክለኛነት፣ ሁሉን አድራጊ ፈጣሪነት፣ . . . ወዘተ መስማት የሚፈልጉ እንጂ ደካማ ጎናቸውን እንደማንኛውም አንድ ሰው ስህተት መስራታቸውን፣ ተስተካክሎ ተዘጋጅቶ የተሰጣቸውን ከማንበብ በስተቀር ከሌሎች የተለየ ልዩ ተሰጥኦ የሌላቸው መሆናቸውን፣ እነርሱ ሊሰሩ የሚችሉትን ሌሎችም የአገሪቱ ዜጎች ሊሰሩ መቻላቸውን፣ አምባገነንታቸውን፣ . . . ወዘተ መስማት አይሹም።

ስለዚህ በእነርሱ አካባቢ የሚገኙ የበታች ባለስልጣናት የአገሪቱ ዜጋዎች የሆኑ ያለውን መንግስት በመቃወማቸው ያለው መንግስት እንዲታሰሩ፣ እንዲሰቃዩ፣ እንዲገደሉ እርምጃ ከወሰደ በኋላ የወሰደው እርምጃ ትክክለኛ መሆኑን በማግስቱ የአገሪቱ ዜጎች በየአደባባዩ እየወጡ በግዴታ ውዴታ ሰልፍ ላይ በመገኘት ተጽፎ ተዘጋጅቶ የሚሰጣቸውን መፈክሮች በመያዝ፣ በሉ የተባሉትን እያሉ ያረጋግጣሉ።

ከዚህ በኋላ በየመገናኛ ዘዴዎቹ የአገሪቱ ዜጎች መንግስት የወሰደውን እርምጃ በታላቅ አድናቆት እንደደገፉ በማድረግ በየቦታው በግዴታ የተሰለፉትን ሰልፈኞች ቁጥር በማጋነን ይዘረዘራል።

ለእኛ የማይገባን በአንዳንድ አገሮች የነበሩና ዛሬም ያሉ መሪዎች አገሪቱ ውስጥ የሆነ የሕዝብ በዓል ሲከበር የእነርሱን ፎቶግራፍ በበዓሉ ላይ የሚገኘው ሕዝብ ተሸክሞ እንዲሄድ መደረጉ ነው።የአንድ አገር የነጻነት ቀን በሚከበርበት ቀን ለዚህ ሁኔታ

በግዜው ፎቶግራፉ እንዲያዝ የሚደረገው መሪ ምንም አስተዋጽዖ ያላደረገም መሆኑ እየታወቀ፣ በበዓሉ ላይ የሚገኙት ተሳታፊዎች ፎቶግራፉን ይዘው ያለእሱ አገሪቷ እንደማትኖር እየተደረገ በመስበክ፣ የሰልፉ ግዜ እስከሚያበቃ እንዲዞሩ ይደረጋል።

ለምን የራሳቸውን ፎቶግራፎች ይዘው እንዲዞሩ አልተደረገም? ወይስ አገር ማለት፣ ነጻነት ማለት የአገር መሪው ብቻ ስለሆነ ነው? ይህም አልበቃ ብሎ የአገሩ ሰፊው ሕዝብ በረሃብና በበሽታ ሲሰቃይ ሺዎች ብር በማዋጣት የአገሪቱ መሪ ሃውልት በእምነ በረድ ይሰራል። የእንደዚህ ዓይነት የአገር መሪዎች ደካማ አስተሳሰብ እጅግ ያሳዝናል።በእነርሱ ቤት ሕዝቡ ምንም አያውቅም።ግን ሃቁ ሕዝቡ ሁኔታውን ቢያውቅም፣ ሁኔታውን ለመለወጥ በመንግስቱ የሰለጠኑትን አፋኝ ሃይሎች ሊቋቋማቸው አይችልም።ስለሆነም እንደማያውቅ አንገቱን ደፍቶ በእሱ ስም እየተለፈፈ፣ በእሱም ላይ ግፎች ሲፈጸሙም፣ እንዳላየ በመሆን የእሱ ግዜ እስከሚመጣ ድረስ መኖርን ይመርጣል።

ባጠቃላይ ለአንድ አገር መሪም ሆነ ለሌላ ግለሰብ በብዙ ሺ ብር የሚቆጠር ገንዘብ አውጥቶ ሃውልት መስራቱ፣ በእርግጥ በአገሪቱ ዜጎች ሃብት መቀለድ ካልሆነ፣ ጠቃሚነቱ ለእኛ ፈጽሞ አይታየንም። የመሪውን ሃውልት እንደ ጣኦት የአገሩ ህዝብ ሲያልፍ ሲያገድም እንዲሳለመው ከሆነም፣ ባገሩ ውስጥ ያሉት መስጊዶችና ቤተ ክርስቲያኖች የተሻሉ ሳይሆኑ አይቀሩም ብለን እናምናለን። የህብረተሰብዓዊንትን ርዕዮተ ዓለም ተቀብለናል የሚሉትን አገሮች አብዛኛዎቹን ስንመለከት፣ መሪዎቻቸው አንዴ ስልጣን ከያዙ በኋላ እስከ እለተ ሞታቸው ስልጣኑ ላይ ሙጭጭ እንደሚሉ ቀደም ብለን ገልጸናል።

ይህ ብቻ ሳይሆን በአገራቸው ውስጥ ከእለት ወደ እለት የእነርሱ ፎቶግራፎች፣ ሃውልቶች፣ በእነርሱ ስም የሚጠሩ ትምህርት ቤቶች፣ ሆስፒታሎች፣ . . . ወዘተ ቁጥራቸው እየጨመረ ይሄዳል። በአገራቸው ውስጥ በሚካሄዱት በዓላት በሙሉ የእነርሱ ፎቶግራፎች ተይዘው ስለእነርሱ የሚነገሩ ሰበካዎችን ከማሰማት ሌላ ስለ በዓሉ ታሪካው አመጣጥ ብዙም አይነገር። የህብረተሰብዓዊነትን ርዕዮተ ዓለም በማይቀበሉ አንዳንድ አገሮችም ውስጥ ደግሞ ይህ ሁኔታ ታይቷል። ዛሬም እየታየ ነው።

የንጉሳዊ ቤተሰቡ ታሪክ በትምህርት ቤት ደረጃ ሲሰጥና ስለእነርሱ ሰውነት፣ ገናናነት፣ . . . ወዘተ እንጂ ሰፊው የአገሪቷ ዜጎች የሚሻሻሉበትን ሁኔታ የሚያስረዳ የትምህርት አሰጣጥ ላይ ብዙም አይተኮርም።የአገሪቷ ትክክለኛ ዜጎች ንጉሳዊ ቤተሰቦች ብቻ እንደሆኑና ሌላው የአገሪቱ ዜጎች ለእነርሱ አገልጋዮች ሆነው እንደተፈጠሩ የሚታመንበት ሁኔታ አለ።

እንደነዚህ ዓይነቶቹ የአገር መሪዎች በጣም ወደኋላ የቀሩና ሕዝቡንም ለማታለል ዘዴያቸው አምቺ ሰላልሆነ፣ ከስልጣናቸው ለማውረድ ብዙ ግዜ የሚፈጅ አይመስለንም።ሆኖም የአገሪቱን ገንዘብ በተቻላቸው ስልጣናቸውን እንደያዙ ለመቀጠል ስለሚፈልጉ ከውጭ ሃይል ጋርም ስምምነት በመፍጠር የአገሪቱን የሰፊውን ሕዝብ ብሶቶች ለማፈን ወደኋላ አይሉም። በዚህና ሌሎችም የተለያዩ ምክንያቶች ስልጣናቸውን ይዘው ለመቆየት ይችላሉ። ችለዋልም።

እንግዲህ ለእኛ የማይገባን የአንድ አገር መሪ መሆን ማለት እዚያች አገር ካሉት ሰዎች ሁሉ የበለጠ እውቀት፣ ስለአገሪቷ የበለጠ ስሜት ያለውና ለአገሪቷ ከማንም በላቀ ሁኔታ የሚያስብ፣ እሱ የሚናገረው ሁሉ ትክክል የሆነና ስህተት የሚባልን ነገር የማይሰራ፣ ወደፊት የሚሆኑትን ወይም የሚፈጠሩትን ነገሮች ሁሉ ከማንም አስቀድሞ የሚያውቅ ነቢይ እንደሆነ ይደረጋል።ለምን አንድ ሰው በዚህ መልክ ይመለካል?

ከተንሳይት በቃና

http://www.ethiopanorama.com